# በስዊዘርላንድ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን በጋራ ያደረጉት የሰላማዊ ሰልፍ በተሳካ ሁኔታ ተከናወነ!

ግንቦት 8 ቀን 2000 ዓ.ም. (ሜይ 16 ቀን 2008) በአውሮፓ የተባበሩት መንግሥታትና ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ በሆነችው በጄኔቫ ከተማ ደማቅ የሰላማዊ ሰልፍ ተካሂዷል። በስዊዘርላንድ ነዋሪ የሆኑ የቅንጅት፤ ሕብረትና የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ(ኢማስ) በጋራ የጠሩት ትእይንተ ሕዝብ ከተጠበቀው በላይ እድምተኛ ከመላው የስዊዘርላንድካን ቶኖች በተሳተፉት በዚህ ከረጂም ጊዜ ቢኋላ (የቅንጅት መሪዎች ከእስር ከተፈቱ ወዲህ) በተደረገ የሰላማዊ ሰልፍ ላይ  ከላይ የተጠቀሱት ማለትም ቅንጅትሕብረትና በስዊዘርላን ድ የኢትዮጵያውያን ማህበር (ኢማስ) በጋራ ያስተባበሩት የተቃውሞ ሰልፍ በብዙ መልኩ ስኬታማ መሆኑ እሙን ቢሆንም የተጀመረው ሕብረት እንቅስቃሴ ወደበለጠ የጋራ ተሳት ፎና መቀራረብ መንገድ ጠቋሚ መሆኑ በእጅጉ ታምኖበታል።

ይኸ በ1997 (2005) ግንቦት ወር የኢትዮጵያ ሕዝብ በምርጫ ካርድ የተቀዳጀውን ድል የወያኔን የግድያ፣ እስር፣ በደልና ግፍም ለመዘከር „The World wide March for Ethiopian Freedom, Human Rights and Justice Organizing Committee“ ማለትም የሃሳቡ አመንጪና ከአስተባባሪዎቹ አንዱ የሆኑት የአኙዋክሕዝቦች ዓለም አቀፍ ተቆርቋሪ ምክር ቤት ሥራ መሪ አቶ ኦባንግ ሜቶ አነሳሽነት በመላው ዓለም ከ ሜይ 15 እስከ ሜይ  18 ድረስ ሊካሄድ የታቀደው የሰላም እንቅስቃሴአካል ነው።

ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ያዘጋጁቸውን ደባዳቤዎችና ፊርማዎች (ፔቲሽን) ለተባበሩት መንግሥታት የአው ሮፓው ዳይረክተር ጄኔራል፣ ለሰብዐዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሜሽነር፣ በተባበሩት መንግሥታት ለስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽነርና በመጨረሻም በተባበሩት መንግሥታት የስዊዘርላንድ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ደብዳቤዎቹ ተሰጥተዋል።

ፎቶዎቹን ይመልከቱ ዝርዝር መግለጫ ከምስሎችና ተንቀሳቃሽ ምስሎች ጋር በቅርቡ ይቀርባሉ።

የሰልፉ አስተባባሪ ግብረ ኃይል